# እንቅልፍ!



በውድቅት ሌሊቱ
ከሞቀው ኣልጋዬ
በወቅቱ፣ በሰዓቱ
ብርድ-ልብስ ደርቤ
ተከናንቤ
ሓሳቤ እሹሩሩ...
ብቻውን ነጐደ!
ያላበው ገላዬ
በቅዠት ዓበደ
እንቅልፍ እንጅሩ!
ስወራጭ፣ ሳልተኛ፣
ስገላበጥ ክፉኛ
ኣጉል ነጋብኛ...
እንቅልፍ የት ኣባቱ
ሄደ...

ቢሮ ገብቼ ግን
ሥራ ሲያፋጥጠኝ
ወይ ስቃዬ!
ሳልሞት፣ በውኔ
ቁጭ ብዬ ወንበር ላይ
ፍዝዝ ይላል ዓይኔ
ኣለቃዬ



ዓይን-ዓይኔን ሲያይ
ወይኔ፣ ወይኔ!
ነቅቶ መቀመጡ
እምቢዮ ይለኛል
ዓይኔን መግለጡ...
ያቅተኛል
ሽልብ ያደርገኛል...
ምን ኣባቱ!

ገ/ኢ. ጐርፉ።